# “ኦሮሞ first” ሰሞነኛዉ የዲያስፖራ ቅጥፈት

(በአዲሱ አረጋ ቂጤሳ 01/06/14)

በአዉሮፓና በሰሜን አሜሪካ አካባቢዎች የሚገኙ አንዳንድ የኦሮሞ ዲያስፖራዎች “ኦሮሞ first” በሚል የተንሻፈፈ አጀንዳ በህዝብ ስም ለመነገድ በዘመቻ መልክ ላይ ታች ሲሉ በቅጥፈታቸዉ ተገርሚያለሁ፡፡ የዘመቻቸዉ ዋና አላማ የኦሮሞ ህዝብ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ከብሄራዊ ጭቆና ያልተላቀቀ፣ ባይተዋር እንደሆነ አስመስሎ ማቅረብ ነዉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ለህዝቡ መብት ለመታገል የተነሱ በማስመሰል ስብሰባዎችን በየቦታዉ እያዘጋጁ “በፖለቲካ ቢዝነስ” የገንዘብ ትርፍ ማግኘት ነዉ፡፡ ይህን ዘመቻ አሳፋሪና አሳዛኝ የሚያደርገዉ የኦሮሞ ህዝብ አለበት ብለዉ ለሚያነሱት የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ “ጭቆናዎች” ሌላዉን ህዝብ ተጠያቂና ጠላት አስመስለዉ የሚያቀርቡ መሆኑ ነዉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ “ኦሮሞ first” የሚለዉን ሃሳብ ለማራመድ የአዉሮፓና የአሜሪካ ታላላቅ ሆቴሎች ትክክለኛ ቦታዎች አይደሉም የሚል ጽኑ ዕምነት አለኝ፡፡ (ምናልባት አዉሮፓ የሚገኙ ሆቴሎች “Europe First” አሜሪካ ያሉት ደግሞ “USA first” የሚሉ አጀንዳዎችን ለማራመድና ተግባራዊ ለማድረግ ትክክለኛ ቦታዎች ሊሆኑ ይችሉ ይሆናል፡፡) ከመነሻዉ “ኦሮሞ first” የሚለዉ አጀንዳ ማራመድ ቢያስፈልግ እንኳ አጀንዳዉን ማራመድ የሚቻለዉ ህዝቡን በማነቃነቅ በኦሮሚያ ምድር በገጠር በአሮሞ አርሶ አደር ማሳ፣ በከተማ ደግሞ በኦሮሚያ ከተሞች ብቻ ነዉ፡፡ ይህ አጀንዳ ባለፉት ሁለት አስርት አመታት በተግባር ተፈትኖ የህዝቡን ተጠቃሚነት በተጨባጭ ያሳየ ባለቤት ያለዉ ጉዳይ ስለሆነ አሁን ደርሶ አጀንዳ ሊሆን አይችልም፡፡ የአዉሮፓና የአሜሪካ ሆቴሎች ማሟሟቂያና ለአንዳንድ ጀማሪ ዲያስፖራ ‘ፖለቲከኞች’ የፖለቲካ አፍ ማሟሻ ሊሆን አይችልም፡፡ በህዝብ ስም ለመነገድ ለተዘጋጁ አካላት የኪስ ማድለቢያ አጀንዳ ሊሆንም አይገባዉም፡፡

በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን ህገ መንግስታዊ መብት ተጎናጽፈዋል፡፡ ስለዚህ ሁሉም ሃገሪቱ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በጋራ መፈቃቀድና ስምምነት በመሰረቷት ሃገራቸዉ first ናቸዉ፡፡ first መሆናቸዉም ተረጋግጠ ህገመንግስታዊ ዋስትናን አግኝቷል፡፡ ስለሆነም በአዲሲቷ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የኦሮሞ ህዝብ እንደማንኛዉም ኢትዮጵዉያን ወንድሞቹ first ነዉ ማለት ነዉ፡፡ ይልቁንም የኦሮሞ ህዝብ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ግንባታ የትግል ሂደት ካለዉ ታሪካዊ ሚና፣የህዝብ ብዛት፣ከክልሉ የቆዳ ስፋት፣ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥና እምቅ የተፈጥሮ ሃብት በሁሉም ረገድ ማለት ይቻላል firstም በላይ መሆኑን በተጨባጭ እያሳየ ነዉ፡፡ ኢትዮጵያንም first እያደረገ ያለ ህዝብ ነዉ፡፡ የኦሮሞ ህዝብ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ የራሱን ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በመመስረት ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጥቅሞቹን አስከብሯል፡፡ ከዚህም አልፎ በፌዴራሉ መንግስት ሕግ አዉጪ፣ ህግ ተርጓሚና ህግ አስፈጻሚ በሆኑ የመንግስት አካላት ዉስጥ በከፍተኛ የሃላፊነት ቦታዎች ላይ እያገለገሉ ያሉት አመራሮች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ ኦሮሞዎች እንደሆኑ፣ እየሰጡት ባለዉ የለዉጥ አመራርም ኢትዮጵያን first እያደረጉ እንደሆነ ማንም ሊክድ አይችልም፡፡ የሃገሪቷን አብዛኛዉን የዉጭ ንግድ በግብርና ምርቶች ላይ እንደተመሰረተ

ይታወቃል፡፡ እነዚህን ምርቶች ባብዛኛዉ የሚያመርቱት የኦሮሞ አርሶ አደሮች ናቸዉ፡፡ አርሶ አደሮቹ በጥራትና በብዛት በሚያመርቱ ቡና፣ ሰሊጥ፣ ቦሎቄ፣ ቁም እንስሳት ወዘተ first ናቸዉ፡፡ ኢትዮጵያንም በዉጭ ንግድ first በማድረግ ላይ ናቸዉ፡፡ ሀገሪቷ ወደ ኢንዱስትሪ መር የኢኮኖሚ ልማት እያደረገች ባለችዉ ግስጋሴም ኦሮሚያ firsተ ናት፡፡ በሀገሪቷ እያበቡ ያሉት እንዱስትሪዎች አብዛኛዎቹ በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ከመሆኑም በላይ በግብኣት ትስስርና በሚፈጥሩት የስራ ዕድል ሕዝቡን ግንባር ቀደም ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ የሃገሪቷ የንግድ እንቅስቃሴ ባብዛኛዉ በኦሮሚያ የሚካሄድ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ኢትዮጵያ በመንገድ፣ በኤሌክትሪክ ሃይል፣ በዉሃ፣ በትምህርት ፣ በጤና ወዘተ በመሰረተ ልማት ግንባታ እመርታ እንዳስመዘገበች መላዉ አለም የሚያዉቀዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ የኦሮሞ ህዝብ በእነዚህ መሰረተ ልማቶች ግንባታ በግንባር ቀደምትነት እየተሳተፈና በላቀ ሁኔታ እየተጠቀመ ነዉ፡፡ ህዝቡ ኦሮሞ first መሆኑን በአዉሮፓና አሜሪካ ሀገራት በሚገኙ ሆቴሎች በሚደረጉ ዲሰኩሮች ሳይሆን በቀዬዉና በህይወቱ እያየዉ ባለዉ ተጨባጭ ለዉጥ ይገነዘባል፡፡ የለዉጡን ምንጭም ጠንቅቆ ያዉቃል፡፡

በኦሮሚያ ገጠሮች ኦህዴድ/ኢህአዴግ ባመነጫቸዉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና በነደፋቸዉ ዕቅዶች መላዉን የኦሮሞ አርሶ አደርና አርብቶ አደር በማነቃነቅ፣ አስፈላጊዉን ምርት ማሳደጊያ ቴክኖሎጂዎችን በማቅርብ፣ የመስኖ ልማትን በማስፋፋት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ የህዝቡን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ ኦሮሞ first መሆኑን በተግባር አረጋግጧል፡፡ ባለፉት ዘጠኝ ተከታታይ አመታት ሀገሪቷ ካስመዘገበችዉ ፈጣን ተከታታይና ሁሉንም ተጠቃሚ እያደረገ በሚገኘዉ የኢኮኖሚ እድገት የአንበሳ ድርሻዉን የሚወስደዉ የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልል እያስመዘገበዉ ያለዉ ዕድገት ነዉ፡፡ይህ ዕድገት በአርሶ አደር ማሳ ላይ በተመሰረተ ግብርና የመጣ ነዉ፡፡ በመሆኑም የኦሮሞ አርሶ አደሮች ያስመዘገቡት ዕድገት እንደሆነና ኑሮአቸዉም እየተመዘገበ ባለዉ እድገት ልክ እየተሻሻለ እንደመጣ አያጠራጥርም፡፡ ድርጅቱ በሰጠዉ አመራር በየገጠር ቀበሌዉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በመክፈት ሕጻናትና ታዳጊ ወጣቶች ከማህይምነትና ከድንቁርና እንዲላቀቁ በማድረግ first አድርጓቸዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በኦሮሚያ ክልል ከ 7 ሚሊየን በላይ ታዳጊ ህጻናትና ወጣቶች በትምህርት ገበታ ላይ ይገኛሉ፡፡ በሀገሪቷ በሚገኙ 33 የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ትምህርታቸዉን በመከታታል ካሉት ኢትዮጵዉያን ወጣቶች አብዛኞቹ የኦሮሞ አርሶ አደር ልጆች ናቸዉ፡፡ በየገጠር ቀበሌዎች ከስድስት ሺህ በላይ የጤና ኬላዎች፣በየገበሬ ማህበሩ የጤና ጣቢያዎች፣ በየወረዳዉ ሆስፒታሎች ተገንብተዉ ለህብረተሰቡ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ገጠር ቀበሌዎችን ከሌሎች ቀበሌዎች የሚያገናኙ ክረምት ከበጋ የሚያሰኬዱ መንገዶች በሚያስገርም ሁኔታ ተገንብተዉ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ለዚህም ከመላዉ የኦሮሞ አርብቶ አደሮችና አርሶ አደሮች በላይ ሌላ እማኝ መጥራት አያስፈልግም፡፡ በከተሞችም በሚሊዮን የሚቆጠሩ የኦሮሞ ወጣቶቾን ከስራ አጥነት በማላቀቅ ከድህነት ወደ ሃብት፣ ከእጦት ወደማግኘት በማሸጋገር first እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ በማድረግም ላይ ይገኛል፡፡

የከሰሩ ዲያስፖራዎች “ኦሮሞ first” አጀንዳን እጅግ በጣም አሳፋሪና ዘረኛ የሚያደርገዉ የኦሮሞ ብሄር ተወላጅ ያልሆነዉን ሌላዉን ኢትዮጵያዊ በዉሸት የኦሮሞ ጠላት አስመስለዉ የማቅረባቸዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ በኦሮሚያ ክልል በብዙ ሚሊየን የሚቆጠሩ የሌላ ብሄር ተወላጆች በሰላም፣ በፍቅርና በአንድነት ይኖራሉ፡፡ በርካታ ኦሮሞዎችም ከኦሮሚያ ክልል ዉጭ በሌሎች የሃገሪቷ ክልሎች በተመሳሳይ መልኩ ይኖራሉ፡፡ ይህ ሀገራዊ አንድነታችንን የበለጠ የሚያጎለብት ከመሆኑም በላይ የዜጎች ህገ መንግስታዊ መብት ነዉ፡፡ አንድን ህዝብ የሌላዉ

ህዝብ ጠላት አስመስሎ ማቅረብ እልቂትን ሊያስከትል የሚችል አደገኛ የሆነ የፖለቲካ አስተሳሰብ ነዉ፡፡ በዚህ አይነት የፖለቲካ አሰተሳሰቦች በመመራት የፋሺ እና የናዚ ፓርቲዎች በአለም ላይ ከፍተኛ የሆነ ዕልቂት እንዳስከተሉ ይታወቃል፡፡ በአለማችን የጀርመኑ ናዚ ፓርቲ የዉስጥ ዉጥረት ሲበረታበት ለጀርመናዉያን ችግር ዋናዉ መንስኤ አይሁዶች እንደሆኑ አስመስሎ በማቅረብ በዘረኝነት ላይ የተመሰረተ እልቂት እንዳስከተለና በድንቁርና የተሞላ ታሪካዊ ስህተት እንደሰራ ይታወቃል፡፡ ዲያስፖራዎቹ ከናዚ ፓርቲ አሳፋሪ ታሪክ በሚመሳሰል መልኩ ለኦሮሞ ህዝብ የፖለቲካ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ችግሮች መንስኤዉ "ሌላዉ ብሄር ኦሮሞን ስለሚጨቁን፣ ሃብቱንም ስለሚበዘብዝ ነዉ" በማለት በየመድረኩ የቅጥፈት ዲስኩር ይደሰኩራሉ፡፡ ሌላዉን ብሄር የኦሮሞ ህዝብ ጠላት እንደሆነ በማስመሰል ለማቅረብ እየሞከሩ ነዉ፡፡ ቅዠታቸዉም ኦሮሚያ ተገንጥላ የኦሮሞዎች ብቻ ሃገር ሆና ማየት ነዉ፡፡ በሽግግር መንግስት ዘመን ኦነግ በኦሮሚያ ክልል ይንቀሳቀስ በነበረበት ወቅት በዚህ ኋላ ቀርና ጸረ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ በኦሮሚያ ክልል ለረዥም ዘመናት ሲኖሩ የነበሩትን ኦሮሞ ያልሆኑ ሰላማዊና ጭቁን ኢትዮጵያዉያንን የኦሮሞ ህዝብ ለዘመናት ሲደርስበት ለነበረዉ ጭቆና ተጠያቂና የህዝቡ ጠላት አስመስሎ ለማቅረብ በመሞከሩ ትልቅ የፖለቲካ ኪሳራ እንደደረሰበትና ከሰፊዉ የኦሮሞ ህዝብ እንደነጠለዉ ሁሉም ሰዉ የሚያስታዉሰዉ ጉዳይ ነዉ፡፡

ማንም የፖለቲካን ሀሁ አዉቃለሁ ብሎ የሚነሳ ፖለቲከኛ "ኦሮሞ first" በሚል የቅጥፈት አጀንዳ በብሄር ሽፋን የዘረኝነትና የጥላቻ ፖለቲካ ከማራመዱ በፊት ኦሮሞን ህዝብ ታሪካዊ ዳራና ፖለቲካዊ ስነልቦና ማወቅ ግድ ይለዋል፡፡ የኦሮሞ ህዝብ በገዳ ስርዓት ያጎለበተዉና የቆየ ዴሞክራሲያዊ ትዉፊት ያለዉ ህዝብ ነዉ፡፡ ጥንት በሚደረጉ ጦርነቶች ወቅት እንኳ የሚማረኩ ወገኖችን በሞጋሳ የብሄረሰቡ አካል ያደርጋቸዋል፡፡ በጦርነት የተማረኩትን ግለሰቦችን በጉዲፈቻ የራሱ ልጅ አድርጎ ይወስዳል፡፡ መሬትና ከብቶች በመስጠት፣ ሴት ልጁን በመዳር የኦሮሞ ብሄረሰብ አባል ያደርገዋል፡፡ ታዲያ ይህን የመሰለ አኩሪ ዴሞክራሲያዊ እሴትና ታሪካዊ ዳራ ያለዉ ህዝብ ለዴሞክራሲዊ አንድነት፣ ለእኩልነት፣ ለፍቅርና ወንድማማችነት አስተሳሰብ ዙሪያ ለማሰባሰብና ለማታገል የተመቸ ነዉ፡፡ በተቃራኒዉ ህዘቡ ከምንም በላይ ሌላዉን ህዝብን እንደ ጠላት መቁጠር እንደ ነዉር የሚቆጥር በመሆኑ ለሰሞነኛዉ የቅጥፈት አጀንዳ ጆሮዉን የማይሰጥ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነዉ፡፡ ስለሆነም የኦሮሞን ህዝብ ከጎኑ ለማሰለፍ የሚያልም ማንኛዉም የፖለቲካ ቡድን የህዝቡን እሴቶች አጀንዳዉ ካላደረገ ሊሳካለት አይችልም፡፡ የህዝቡን ዴሞክራሲያዊ እሴቶች፣ ታሪካዊ ዳራና ፖለቲካዊ ስነ ልቦናን ተገንዝቦ በመንቀሳቀስ የህዝብ ወገንተኝነቱን በተግባር ማሳየት ያልቻለ ፖለቲካ ቡድን ሺህ ጊዜ "ኦሮሞ first" እያለ ሲጮህ ቢከርም በአዉሮፓና በአሜሪካ የሚገኙ ሆቴሎች የሚሪንዳና የኩኪስ ገበያ ከማድራት ያለፈ ፋይዳ ያለዉ ነገር አይሰራም፡፡ ዲያስፖራዎቹ ከህዝብ ፍላጎትና አስተሳሰብ በተቃራኒ ከርቀት እየጮሁ ስለሆነ ያላቸዉ እድል እንደ ኦነግ ከህዝብ ተነጥሎ መቅረት እንደሆነ አያጠራጥርም፡፡

በሃገሪቱ እየተመዘገበ ያለዉ ጅምር የኢኮኖሚ እድገት የእያንዳንዱን ዜጋ ህይወት መለወጥ ጀምሯል፡፡ በጅምር የኢኮኖሚ እድገት ዳይናሚክስ ደግሞ አመራሩን የተሻለ ተጨማሪ እድገት በቶሎ ካላመጣህ ብሎ የሚያስጨንቅ ጠያቂና ለዉጥ ፈላጊ ማህበረሰብ (demanding society) ፈጥሯል፡፡ እነዚህ ዲያስፖራዎች ብልህ ቢሆኑ ኖሮ ይህን ተጨባጭ ማህበረሰባዊ ሁኔታን በመገምገም የተሻለ ልማትና ተጠቃሚነትን በፍጥነትና በጥራት አምጥተን ዋናዉን ጠላት ድህነትን ድል በመንሳት first እናደርጋችኋለን የሚል የተግባር አጀንዳ ይዘዉ ይነሱ ነበር፡፡ የኦሮሞ ህዝብም ጠላቱ ለዘመናት በመተሳሰብ፣ በፍቅርና፣ በወንድማማችነት ለዘመናት አብሮት የኖረዉ የሌላዉ

ብሄር ተወላጅ ወንድሙ እንዳልሆነ በትክክል ያዉቃል፡፡ ጠላቱ እድሜ ልኩን ያሰቃየዉ ድህነት መሆኑን ስለሚገነዘብ እነዚህ ዲያስፖራዎች የተሻለ ልማትና ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ ከድህነት ቀንበር በቶሎ በማላቀቀ first እናደረገሃለን የሚል አጀንዳ ይዘዉ መነሳት ቢችሉ ሚሊዮኖችን ማስከተል በቻሉ ነበር፡፡ ህዝቡ እድገቱን በማፋጠን ዋና ጠላቱ ላይ ሊዘምተዉ የሚችል አማራጭ የፖለቲካ ድርጅት ስለሚያገኝ በትልቅ ደስታ ይቀበላቸዉ ነበር፡፡

የኦህዴድ/ ኢህአዴግ ኦሮሞ first በተግባር ስኬታማ ሊሆን የቻለዉ የኦሮሞን ህዝብ ፍላጎት የሚያስተናግዱ አጀንዳዎችን ይዞ በመነሳቱ ነዉ፡፡ ድርጅቱ የኦሮሞ ህዝብ ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ዘላቂና አስተማማኝ ሊሆን የሚችለዉ በኦሮሚያ ዉስጥ የሚገኙ ሁሉም ብሄር ብሄረሶችና ህዝቦች ከኦሮሞ ህዝብ እኩል first ሲሆኑና ተጠቃሚነታቸዉ ሲረጋገጥ ነዉ ብሎ ያምናል፡፡ይህን እምነቱን ከመላዉ የኦሮሞ ህዝብና በክልሉ ከሚገኙ ኢትዮጵያዉያንን በማነቃነቅ በተግባር በማሳየቱ በዉጤት እየታጀበ በተጨባጭ ለዉጥ ማምጣት ችሏል፡፡ በዚህ አካሄድም የኦሮሚያ first መሆን ኢትዮጵያን first ያደርጋል በሚል ቀና አስተሳሰብና ጽኑ እምነት ሰርቶ በክልሉና በሃገሪቱ ዘላቂ ሰላም፣ ልማትና ዴሞክራሲን ከማረጋገጥ አኳያ አኩሪ የሆነ ታሪካዊ ሚናዉን እየተወጣ ነዉ፡፡

በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች first ናቸዉ፡፡ ኦሮሞ ደግሞ በጣም first ነዉ!!!! ስለሆነም ይህ አጀንዳ ያልበላን ቦታ እንደማከክ የሚቆጠር የፌዝ አጀንዳ ይመስለኛል፡፡